# “የተማረ ይግደለኝ”

መማርና ማወቅ ፣ በተንሰራፋበት
ፍልስፍና ገኖ ፣ ምጡቅ በሆነበት
የግለሰቦች መብት ፣ ነፃነት ባለበት
ሕዝብ አለፍርሃት ፣ ወጥቶ የሚገባበት
ብዙሃኑ እረክቶ ፣ ጠግቦ በሚያድርበት
ከንዲህ ያለው ፀጋ ፣ ከንዲህ ያለው ውበት
የኛም ጥረት ነበር ፣ ለመድረስ ካሉበት ።

ሕዝባችንስ ታዲያ ፣ መች ተኛ አንቀላፋ
የምዕርቡን ፈለግ ፣ ተከትሎ ዳፋ
ዘመን አስቆጠረ ፣ ዕውቀቱን ሲያሰፋ
ግን አልሆነም ለኛ ፣ ብንዳክር ብንለፋ
ትላንት እንዳልነበርን ፣ ገናና እና አንጋፋ
እንኳን ብልፅግና ፣ ነፃነት ሊስፋፋ
ከትላንቱ ዛሬ ፣ ጭራሽ እየከፋ
ከድጡ ወደማጡ ፣ ሆነና ከረፋ
እንኳን ያልጨበጥነው ፣ የጨበጥነው ጠፋ ።

ለመማር መድከሙ ፣ ነጭ ላብ ማፍሰሱ
ከረባት ማሰሩ ፣ ገበርዲን መልበሱ
መብለጭለጭ ከሆነ ፣ ክብርና ሞገሱ
መማርና ማወቅ ፣ ከሆነ ለከርሱ
ከእንሰሳት ማነሱን ፣ መች አወቀው እሱ!
ተምረናል ባዮች ፣ አገርን ሲያፈርሱ
ወጣት አዛውንቱ ፣ በምሬት ሲያለቅሱ
ለተገፋ ወገን ፣ ፈጥነው ካልደረሱ
ለስጋው ካልረባ ፣ ከፍ ሲል ለነፍሱ
መማር ምን ያደርጋል ፣ ከንቱ መኮፈሱ
አገርና ወገን ፣ ትርጉም ካጡ ለሱ ።

ገና ድሮ ገና ፣ በልጅነታችን
በናት አገር ፍቅር ፣ ሲቃጠል ልባችን
እያሞጋገስን ፣ ጥንታዊ ጀግኖችን
ለሃገር ቀናዊ ፣ ሆኖ ምኞታችን
ከፍታን ስንመኝ ፣ ከያዝነው በጃችን
ያልተማሩ አባቶች ፣ ያቆዩአትን ሐገር
ከነሱ በላቀ ፣ ከፍ አርገን ለማክበር
“የተማረ ይግደለኝ” ፣ ብለን እንል ነበር
ከቁብ ያልቆጠርነው ፣ ከተረት በስተቀር
ባናውቀው ነው እንጂ ፣ ለካስ ሟርት ነበር
መሃይም ያቀናት ፣ ያስከበራት ድንበር
በተማረው ፈርሳ ፣ ሞታ እንዴት ትቀበር ?

ታዛቢው
March 23, 2018